# የዛሬ እይታ ለነገ፡- እውነት፥ አንድነት፥ ብልጽግና

በቅድሚያ በሚከተለው ጥቅስ ውስጥ የታመቀውን እውነት ያስተውሉ፡-

"እናንተስ አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት፥ ጽድቁንም ፈልጉ፤ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል።" ማቴ. 6፡33

ይህ ጥቅስ የሚያመለክተው፥ አስቀድማችሁ ጥሩዎች ብትሆኑ፥ ለምድራዊ ኑሮአችሁም ቢሆን፥ ተመጣጣኝ ተድላና ደስታን ታገኛላችሁ ማለት ይሆናል። ሰዎች ጥሩዎች ሲሆኑ የእግዚአብሔርም መንግሥት መሬት እንደወረደ ይቆጠራል፤ ጥሩዎች ስንሆን፥ ለነፍሳችን ደስታ እንደሆነ፥ ለሥጋችንም እንዲሁ ይሆናልና። በእግዚአብሔር ፊት ጥሩ ሆኖ መገኘት ጽድቅ ነውና፤ ጥሩ መሆን ጥሩ ያሳስባል፥ ጥሩም ነገር ያስመለክታል። ጥሩነት ብዙ ዘርፍ ስላለው፥ በብዙ መንገድ ይገለጻል፤ አብሮነትም አንዱ ነው። በአብሮነት ሠርቶ በአብሮነት መበልጸግ እንጂ፥ በግለኝነት መበልጸግ መጨረሻው ጦርነት ነው። በብቸኝነት ከሚያድግ ብልጽግና ጋር የሚያድግ የዘረኛነት ኃጢአት መጨረሻው ድህነት እንጂ ብልጽግና አይሆንም - ሃዘንን እንጂ ደስታን አያመጣም። የምትፈልጉትን ሁሉ እንድታገኙ አስቀድማችሁ ጥሩዎች ሁኑ - ሰውን ሁሉ በፍቅር አቃፊዎች ሁኑ እንጂ ዘረኞች አትሁኑ።

ከሁሉ አስቀድመን አንድነታችንን እንሻ፤ አንድ ላይ ብናስብ፥ ጥሩነታችን ይገለጻል፤ ጥሩነታችን ሲገለጽ ሕብረት ይኖረናል፤ በአብሮነታችን "ለጋራ ብልጽግና" ስንሠራ ነው የምናድገው። ከሥልጣኔ እና ከብልጽግና የሚቀድመው ሕብረትና አንድነት ነው። በከበደ ሚካኤል የተጻፈው "ጃፓን እንደምን ሠለጠነች?" የተሰኘውም መጽሐፍ የሚያመለክተው ይህንኑ ነው። ኢትዮጵያችን እንዲህ እንዳሁኑ ተከፋፍላ ልታድግ - ልትበለጽግ አትችልም።

ብዙ ምድራዊ እውቀት የሌላቸው ብዙሃን በውስጣቸው ያለውን እውነት ገልጠው የሚያስረዱበት ባህረ ሃሳብ ቢያጥራቸውም - የእውቀት ድሆች ቢሆኑም - የእውነት ማህደሮች በመሆናቸው በፍቅር፥ እምነትና በተስፋ ይኖራሉ፤ ጥሩውን ብቻ እያስተዋሉ። "ሁሉ ይጨመርላችኋል" እንዲል የጥሩነታቸው ክስተት የሚፈልጉትን አያሳጣቸውም። ያለንን ትንሿን ተካፍለን መብላት ብናውቅበት፥ በስምጥ ሸለቆ ከርሰ ምድር የታመቀ ኃይል (geothermal power) እና በኦጋዴን የተከማቸ ነዳጅ ብቻ ሊያበለጽጉን ይችላሉ። በተረፈ፥ ያ የምናስበው ድሎት - ብልጽግና (እድገት) በቅጽበት የማይመጣ፥ ጊዜ የሚወስድ የሶሻልና የኢኮኖሚ ክስተት ስለሆነ፥ በፍቅር ሰንሰለት ተሳስረን ኢትዮጵያችንን በአንድነት ለማሳደግ ስንነሳ ነው ሁሉም ነገር ጥሩ የሚሆን።

በምድራችን ብዙ የሚያውቁ አዋቂዎች በውስጣቸው ግን እውነት የሌላቸው መሪዎች - ጸሓፊዎች ተናጋሪዎች - ሰውን ሁሉ ዝም ማሰኘት ይችላሉና፤ ከሰው የምትሰሙት፥ ከጽሑፍም የምታነቡት በውስጣችሁ ያለውን እውነት ይቀስቅስ እንጂ፥ የስነ አይምሮአችሁን የአስተሳሰብ ችሎታ በሌሎች ላይ አታስደግፉት - ይጥላችኋል። ከእውነተኛ ሰው እውነት ምንጊዜም አንድ ወጥ - የእውነት ስነ አመክንዮም አንድ አይነት እንደሚሆን ሁሉ፥ የሰውን "የልቡን" ከንግግሩ እና ከሥራው እየለያችሁ፥ ለእናንተ የሚመጥነውን ሃሳቡን ብቻ ውሰዱ እንጂ፥ ማንንም አትመኑ - ለምድራዊ ድሎት ስትስገበገቡ፥ በማታውቁት ውስጥ ገብታችሁ ሰውን ስትከተሉ - እውነተኛ ደስታችሁን እንዳታጡ።

ሰውን በሰውእነቱ የሚያስተሳስር፥ ሰብአዊ አስተሳሰብ ነው ቅድሚያ ማግኘት ያለበት፤ ቀሪው ተቀጽላ ነው። አገራችን አያሌ ጠቢባንን አፍልቃለች፤ ግን የ106 ፓርቲዎች መኖር የሚያንጸባርቀው የግለኝነትና የሥልጣን ጥም ድንቁርና ምን ያህል ባገራችን እንደተንሰራፋ ነው። አሁንም በአስተሳሰባቸውና በሥራቸው ሁሉ ከዘረኛነት ኃጢአት ያልተላቀቁ ይኖራሉ። ያ የርኩስ መንፈስ ተምሳሌት የሆነ የኖሌ ሃውልት አሁንም በአርሲ ተገትሮ ይሳደባል። የእነኚህ የ106 ፓርቲዎች አቋም ምንድነው በኖሌ ሃውልት ላይ?

ከሰው - ከመሪ (ከፓርቲ) እውነትን ፈልቅቆ ማውጣት ያን ያህል ከባድ ላይሆን ይችላል። ለእውነተኛ ዲሞክራሲ ቆሜአለሁ የሚል ፓርቲ እንዴት ነው ያንን "እውነተኛ" የሚለውን ዲሞክራሲ ወደ ሰፊው ሕዝብ የሚያዳርሰው፥ ጠላቱ ካልሆነ ኢትዮጵያዊ ወገኑ ጋር አብሮ መክሮ ዲሞክራሲያዊ ያልሆነውን ኃይል በተባበረ የምርጫ ኃይል ሳያሸንፍ?

አገራችን አያሌ ጠቢባንን አፍልቃለች፤ ግን መንገዱን ሁሉ ዝግትግት ያደረገው የውስጣዊ ባህሪ ክፋት (ውሸት፥ ራስን ወዳድነት የሥልጣን ጥም...) ሆኖ ነው እንጂ፥ ስርዓተ መንግሥትን ከሰፊው ሕዝብ አውጥቶ ለሰፊው ሕዝብ ማስረከብ ያን ያህል ከባድ አይሆንም ነበር።

ኢትዮጵያችን እንዲህ ተከፋፍላ ልታድግ - ልትበለጽግ አትችልም፤ ሕዝቦችም ሥጋዊ ተድላና ደስታን አያገኟትም አስቀድመው ካልተባበሩ ለጋራ ብልጽግናም አብረው ካልሠሩ። ይህንን የማይረዳና የማይገነዘብ የፖለቲካ ፓርቲ ኢትዮጵያችንን አይጠቅማትም። አገራችን አያሌ ጠቢባንን አፍልቃለች፤ ግን ከሁሉ አስቀድሞ ለኢትዮጵያችን የሚያስፈልጋት አንድነት መሆኑን የሚያሳውቁ ፖለቲከኞች

ጥቂቶች ናቸው። አንድነትን ከሚሰብኩ ጎን የሚሰለፉ ጠቢባን እና እውነተኞች ናቸው። በኢትዮጵያዊነት አብሮ ማሰብን ስንጀምረውና ስናዘልቀው መጨረሻውም ጥሩ ይሆናል።

እውነት ምንጊዜም አንድ ወጥ - የእውነት ስነ አመክንዮም አንድ አይነት ነውና የሚሆነው፥ ከእውነተኛ ሰው (ከእውነተኛ ፓርቲም) ለሰፊው ሕዝብ እንደ እውነት የሚቀርበውን ከፓርቲው አጀንዳ መመርመር ግድ ይላል። ለምሳሌ፡- በኢሕአደጎች የፖለቲካ አጀንዳ ውስጥ እንደ ዋነኛ ነጥብ የቀረበ፥ ኤርትራን ከኢትዮጵያ መገንጠል ነበር፤ እንዳሰቡት ሆነላቸው። ቀጥሎም፥ ልክ እነርሱ እንደሚፈልጉትና እንዳቀዱት ሕገ መንግሥትን አርቅቀው፥ ብሔራዊ ፌደራሊዝምን መሠረቱ። ማነው (የትኛው ፓርቲ ነው) ይህንን በዘረኛነት የተዋቀረ መንግሥታዊ ስርአት በእኩልነትና በነጻነት ላይ በተመሠረተ አንድነትና ዲሞክራሲ ለመቀየር የተነሳ? ይህንንም በፓርቲው አጀንዳ ላይ ያሠፈረ????

ሰውን በሰውእነቱ ከሚያስተሳስር፥ ሰብአዊ አስተሳሰብ ባሻገር ርዕዮተ አለሙንም እንመርምር፤ የሰውን ልቡን ማወቅ ባይቻልም፥ ለሰፊው ሕዝብ እንደ እውነት የሚቀርበውን አጠቃላይ ፍልስፍና ከፓርቲ አጀንዳ መረዳት ይቻላልና።

ከውጪ ፖሊሲም ባሻገር፥ አገራችን በሶሻል፥ በፖለቲካና በኢኮኖሚ የምትመራበትን ርዕዮት በፓርቲያቸው አጀንዳ ውስጥ ለሰፊው ሕዝብ እንዲገባ አድርገው ያስቀመጡ፥ ከነኚህም መካከል ሁሉን አቃፊ የሚመስሉ ይኖራሉ።

ከፍልስፍናው ጀምሮ አላማና ግቡን ቁልጭ እድርጎ በፅሑፍ በማስቀመጥ በግልፅ ያሳወቀ፤ ለኢትዮጵያችን የቆመ መሆኑን ያረጋገጠ (ብሔርን ሳይለይ ሁሉን የሚያሳትፍ) ፓርቲ ማነው?

ፓርቲዎቻችን እውነት ቢኖር ከውስጣቸው - እርስ በርሳቸው ቢናበቡና ጭብጥ በሆኑ ተቋሞች ቢከፋፈሉ ከሦስት አበይት ፓርቲ በለይ አይኖርም ባገራችን። ከኢሕአደግ የወጣውም ለመሠረታዊ ለውጥ የሚተጋ ቢሆን ራሱን ከሌላው ጋር ማዛመድ (አብሮ መሥራት) አያቅተውም። ጥንትም ሕዝባችንን ከሚወክል አካል ስላልወጣ፥ ከሕዝቦች ሁሉ የተውጣጣ ጊዜያዊ የሽግግር መንግሥት (ጊዚያዊ ሕዝባዊ መንግሥት) ነው የሚያስፈልገን ሲባል ቆየና፥ አሁን ያሉንን ኃያላን ሁሉ የሚያስንቅ እርሱ (ከኢሕአደግ የወጣው) ብቻ ሆኖ ተገኘ። አዎን! ልክ እንደተባለውም ባሁኑ ወቅት ጊዜያዊ የሽግግር መንግሥት አደገኛ ሊሆን ይችላል። ግን፥ አሁንም ሕዝቦች ስልል ባለ ድምጽ ይጮሃሉ። “ከልብ ካለቀሱ እንባ አይገድም እንደሚባለው ሁሉ፥ ይህም መንግሥት (ከኢሕአደግ የወጣው) ሥልጣኑን ለብቻው ለመጨበጥ አቅዶ ካልሆነ በስተቀር፥ በኢትዮጵያችን ያሉትን ኃይላት ማስተባበር - ወደ ሦስት ታላላቅ ኃይላት (ፓርቲዎች) ማምጣት አያቅተውም..” ይላሉ። ታዲያ፥ ይህንን ሳያደርግ ቢቀር፥ ልክ በአሁኑ ሁናቴ ያሉ ኃይላት ተሰልፈው ነው ምርጫ የሚካሄደው? ልክ እንደ ቀድሞው - በአንድ ኃያል ፓርቲ አቀናባሪነት? እንዴ! እንዴ! እንዴ! እንዴ! እንዳው ዝም። በሪፎርም መሠረታዊ ለውጥን አገኘን ሲባል - ከድጡ ወደ ማጡ።

እውነተኛ ሰው ሳያስበው ከስህተት ላይ ቢወድቅ ጸጸት ይሆንበታል። ኢሕአደግ ከአዲስ አበባ ቤተ መንግሥት ተባረረ ተባለ እንጂ፥ አሁንም በኢትዮጵያችን ሁሉ አለ ከነ ሰንኮፉ። በጥሩ የተቀሰቀሰ አዎንታዊ አስተሳሰባችን እንዳይጨልምብን እና ተስፋ እንዳንቆርጥ ሰጋን። አሉታዊ ከመሆን አዎንታዊ መሆን ይሻላል በማለት፥ ከሪፎርም መሠረታዊ ለውጥን ስንጠብቅ ቆየን፤ አሁንም ሕዝብና መንግሥት አንድ ላይ ቢያስብ ቀኑ አልመሸም። ቆራጡ የትግራይ ሕዝብ ግን አይን አይናቸውን እያየ ዝም ብሎ አልተቀመጠም (የእነኛን)። ስለዚህ፥ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ኢሕአደግ ከመቀሌ ይፈነቀላል። “ቀጣዩ ምን ይሆናል?” ብሎ ማሰብ የሁላችንም የቤት ሥራ መሆን አለበት።

የእውነተኛውን የትግራይ ሕዝብ መንፈስ የሚከተል ማነው? እውነተኛ የትግራይ ሕዝብ ከእውነተኛ የኤርትራ ሕዝብ እንደማይለይ ሁሉ፥ ከተቀረውም ከኢትዮጵያ ሕዝብም አይለይም። ከእውነተኛ የለውጥ አፋፍ ላይ ነን። በኢትዮጵያ ሕዝቦች መካከል የነበረና ያለ አብሮ የመኖር ታሪክ (ደጉም ክፉውም) አሉታውያን የማያዩት አዎንታውያን የሚታያቸው ታላቅ የአንድነት ኃይልን ሰጥቶናልና፤ መጪው ጊዜ ጥሩ ነው የሚሆን “ለእኛ”።

አገርን ያህል ነገር ለአንድ ፓርቲ (ወይም ለአንድ መሪ) ለቆ ዞር ማለት አይቻልም። ግን፥ ታሪኮች - መረጃዎች- ሃቆች - እውነቶች - ባጠቃላይ እውቀቶች ሁሉም ተደማምረው ኢትዮጵያችንን ከፍ ካላደረጓት፥ በእርቅ፥ እርስ በርስ በመተሳሰብ፥ በአንድነትና በሕብረት ወደፊት ካላራመዷት፥ የፖለቲከኞቻችን ጩኸት - ውጤቱ የኢያሪኮ ግንብ ነው የሚሆን።

ይልቁንም፥ ከዚህም ከዚያም እንቅፋት ሲበዛ፥ በተለይ የብሄር ፖለቲካን ከሚሰብኩ - ተማርን ከሚሉ “ምሁራን” ዘንድ የማይጠበቀው - ኢትዮጵያችንን የሚከፋፍል፥ አንድነቷን የሚያሳጣ ልፈፋ በድግግሞሽ ሲሰበክ፥ ጠላት ከውጭ ሀገር “እኛን” ለመበታተን ሲያሴር፥ ከንቱ ነው “ኢትዮጵያ - ኢትዮጵያ” እያሉ መጮህ - አህጉራዊ አንድነትን አለማስቀደም።

በምክንያት የተቀሰቀሰ በምክንያት ከዚህ ደርሷልና፤ “አብን” እና “ፈንቅል”ን ያቆራኘ አስተሳሰብ በሌሎችም ዘንድ ይኖራልና፥ ያገሬ ሰው ተነስ - አንድነትን ፍጠር - ሕብረትክን አጠናክር። ትኩረትህ ከምታየው የፖለቲካ መሪ አስተሳሰብ ባሻገር ያንተ ንጹህ ልብ - ቀናው አስተሳሰብህና እውነተኛነትህ ነውና፤ ይህቺን የዛሬይቱን ቀን ተሻግረሃት ሂድ፤ የወደፊቷን ኢትዮጵያችንን አስባት።

የኢትዮጵያችን ሰንደቅ አላማ (ባንዲራ) ቀለማት ከሦስት እንደማይበልጥ ሁሉ - የሦስቱ (አረንጓዴ፥ ቢጫና ቀይ) በሕብረት አንድ ላይ ሆኖ መታየትም እንደሆነ - “ይህ ነው የነጻነታችን አርማ” እንድንል ያደረገን፥ ፓርቲዎችም ጭብጥ በሆኑ ተቋሞቻቸው ቢከፋፈሉም ከሦስት የማይበልጡ ቢሆን ነው ሁሉንም ባይምሮአችን ማስተናገድ የምንችል። ሁሉም እውነተኞች ቢሆኑ፥ ሊከፋፍላቸው የሚችል በኢኮኖሚ ስርዓቶች ፍልስፍና ላይ ነው የሚሆን፤ ይኸውም- ሶሻሊዝም፥ ካፒታሊዝም እና ሁለቱንም የሚመስል። ታዲያ፥ እንዲህ ጥርት ባለ ተቋም ላይ ሲሆን፥ ፉክክርና ፉክቻ ቢኖርም በዲሞክራሲ ይዘለቃል።

ባይምሮአችን ማስተናገድ የምንችላቸውን ፓርቲዎች እንደ ነጻነታችን አርማ ቆጥረን ወደፊት እንጓዛለን። ከእውነተኛ የለውጥ አፋፍ ላይ ነን። ኢትዮጵያችን 106 ፓርቲዎችን ታስተናግድ ዘንድ ውሸት አልነገሠባትምና፥ እናንት ለራሳችሁ ብቻ ብላችሁ እንጂ ለኢትዮጵያችን ብላችሁ ያልቆማችሁ ዞር በሉ።

ጊዜው አሁን ነው፤ ከኦሮሞው ከትግሬው ከሌላውም የኢትዮጵያ ብሔር ተገንጥሎ ብቻውን ለመዝለቅ ያቀደ አማራ ኢትዮጵያዊ አይደለም። ከአማራው ከትግሬው ከሌላውም የኢትዮጵያ ብሔር ተገንጥሎ ብቻውን ለመዝለቅ ያቀደ ኦሮሞ ኢትዮጵያዊ አይደለም...ወ.ዘተ.።

ለተበደለ ሰው ሁሉ መቆርቆር ሰብአዊነት ነው። ከሁሉ አስቀድሞ፥ ሰው በዚች ምድር ላይ ሲገኝ ሰው ነበረ፥ ዘር የመጣው በኋላ ነው። ካሁን በፊት በአማራ ላይ የደረሰ በደል - ጭቆና - ግፍ አማራ የሆነውን ሁሉ በአንድ ስሜት ሊያስተሳስረው ይችላል። ልክ እንደዚሁ፥ ካሁን በፊት በሌሎች ላይ የደረሰ በደል - ጭቆና - ግፍ ሌሎችንም በአንድ ስሜት ሊያስተሳስራቸው ይችላል። ይህ ዘረኛነት አይደለም - ለወገን መቆርቆር እንጂ። ግን ብዙ ሰዎች ያልተረዱት - ዘረኛነትን ባልታወቀ ውስጣዊ ሕጋዊ መስተዳድር (ክልል) እንዲጸድቅ ያደረገ መንግሥት (ከአንቀጽ 39 ጋር)፥ የዘረኛነት ባህሬ የሌለበትን ዜጋ በአስተሳሰቡ (በጠባዩ) ሁሉ ወደ ዘረኛነት እየተገፋፋ እንዲሄድ ማድረጉን ነው።

ይህ በሚያውቀውም በማያውቀውም ጉዳይ ተነሳስቶ ሲታገል - ሲታገል ከዚህ የደረሰ ሕዝብ “እኔ እራሴን ሆኜ እንደልቤ በነጻነት መኖር ካልቻልኩ፥ ኢትዮጵያ ትቅርብኝ ብቻዬን እሆናለሁ” እንዲልም የሚገፋፋ ተንኮልን ያቀፈ ሕገ መንግሥት በዲሞክራሲ ስም ተስተካክሎ ተቀምጧል (በማር የተለወሰ መርዝ)። ይህንን አይቶ እንዴት ዝም ይላል ሰው? ማንም ሰው የሆነ ፍጡር በሰውእነቱ በማንኛውም መንገድ ክብሩን፣ ህልውናውን የማስጠበቅ ግዴታ አለበት።

ባሁኑ ወቅት፥ “እኔ ኢትዮጵያዊ አይደለሁም፤ ስለዚህ መገንጠል አለብኝ፤...” ከሚል አፈንጋጭ በስተቀር፥ የተቀርውን ሁሉ ታሪክ ያስተሳስረዋል። በኢትዮጵያችን ታሪክ ውስጥ (ኢትዮጵያችንን በነፃነቷና በአንድነቷ ጸንታ እስከዛሬ እንድትቆይ ያደረገ) አንድ ብሔር ብቻ አይደለም። ሁሉም በሁሉም ዘንድ የደረሰ ነውና፥ ይቅር እንባባል። እስከ ዛሬ በኢትዮጵያችን ላይ የተሠራውን የዘረኛነት ኃጢአት የሚደመስስ እርቅ ነውና፤ በእውነት ከልባችን እንታረቅ፤ ለራሳችን - ለኢትዮጵያችን ብለን።

ከእውነተኛ የለውጥ አፋፍ ላይ ነን። አገርን ያህል ነገር ለአንድ ፓርቲ (ወይም ለአንድ መሪ) ለቆ ዞር ማለት ክህደት ነው። ከያለበት ከብሶት የተቀሰቀሰውን ትግል ሁላችንም በአዎንታዊነት ተመልክተን ወደፊት እንጓዝ። ከእንግዲህስ ለመሠረታዊ ለውጥ ከፉውን አስተሳሰብ መፈንቀል እንጂ፥ ሰውን ማፈናቀል አይደለም። ሕዝቦች መሠረታዊ ለውጥን ይሻሉ፤ የሕዝቦችን ብሶት የሚሰማ ደግ መንግሥት ይመጣል።

“እናንተስ አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት፥ ጽድቁንም ፈልጉ፤ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል።” ማቴ. 6፡33